# 18ኛው የብሄር ብሄረሰቦች ቀን በዓል በድምቀት ተከበረ።

አዲስ አበባ፣ ህዳር 25/2016 ዓ.ም፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን፣ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች አስተዳደር ጽህፈት ቤት እና የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አመራሮችና ሰራተኞች 18ኛው የብሄር ብሄረሰቦች ቀን "ብዝሀነትና እኩልነት ለሀገራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል ህዳር 25/2016 ዓ.ም በተለያዩ ዝግጅቶች አክብረዋል።

ወቅቱ ከመራራቅ ይልቅ በመቀራረብ ከሀይል፤ ከጦርነት ይልቅ የሰላም መንገዶችን በመፈለግ ልዩነትን በአንድነትና በመተጋገዝ ችግሮችን በምፍታት ወደብልፅግና የምንሻገርበት ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ፕሬዝዳንት አቶ ታረቀኝ አስፋው በመክፈቻ ንግግራቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

አያይዘውም ብሄር ሰው ሰራሽ አይደለም ተፈጥሮዊ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ ወደብልፅግና ሊያሻግሩን የማይችሉትን ትርክቶች በመተው ካለፈው ትውልድና ስርዓቶች መልካሙን በመውሰድ ተባብርንና ተከባብረን ጠንካራ ሀገረ መንግሥት መገንባት እንችላለን ብለዋል።

የመወያያ ሰነዱን ያቀረቡት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ዳኛ ወ/ሮ ህይወት ደጉ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲተዋወቁ ፣ የዕርስ በዕርስ ባህል ልውውጥ እንዲያደርጉ ፣ውብ የባህል የፌደራሊዝም ስርዓት ህዝቦች እሴታቸውን ፣ ቋንቋቸውን ታሪካቸውን ፣ ተፈጥሮአዊ ፀጋቸውንና ልዩ ባህላዊ ትርክቶቻቸውን በማስተዋወቅ የማይናድ ህብረ ብሄራዊነታቸውን የሚያጠናክሩበት እንዲሁም ወንድማማችነትን በማጠናከር አንዳችን ለአንዳችን አስፈላጊ በመሆን ለሀገራዊ አንድነት የበኩላችንን አስተዋፅኦ ማበርከት ይገባል ስለ ተናግረዋል።

ውብት በሆነው ልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነት በማጎልበት በሀገራችን ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው የሀገሪቱን ብልጽግና ለማረጋገጥ የተጀመረውን ጉዞ አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል ሲሉ በውይይቱ የተሳተፉ አመራሮችና ሰራተኞች ተናግርዋል።


ስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ፍርድ
ች ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ፅ/ቤት የሚሠሩ
ተግባራት ስታንዳርድ መግለጫ
ሥራዎች አመራር ሁኔታ
የቀረበ አጭር ገለፃ



## ዓለም ማቀፍ ፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ቀን በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ ዋለ።

አዲስ አበባ፣ ህዳር 24/03/2016 ዓ.ም፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን፣የማህበራዊ ፍርድ ቤት እና የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ሰሚ ጉባዔ አመራሮችና ሰራተኞች በዛሬው ዕለት አለም ዓቀፍ የኤች አይ ቪ ኤድስ ቀን **“የማህበረ ሰብ መሪነት ለላቀ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከል” በሚል መሪ ቃል** በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችና በፓናል ውይይት በጉባዔዉ አዳራሽ አከበሩ፡፡

የመግፈቻ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ፕሬዘዳንት አቶ ታረቀኝ አስፋው በሀገራችን ለ35ኛ ጊዜ የሚከበርው አለም ዓቀፍ የኤች አይ ቪ ኤድስ ቀን መከበሩ መንግስት በሽታውን ለመከላከል ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል፣ ስለዚህ ይህን የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ የድርሻችን ልንወጣ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ስልጠናውን የሰጡት ከልደታ ጤና ጣቢያ የመጡት ባለሙያዎች አቶ ሙሉጌታ አስናቀው ና አቶ ታከለ ጋሹ እንደገለፁት የኤች አይ ቪ ኤድስ ቀን በዓለም ለ36ኛ ጊዜ በሀገራችን ለ35ኛ ጊዜ የሚከበር መሆኑን ጠቅሰው አሁን ባለው ወቅታዊ መረጃ በኢትዮጲያ ያለው የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት እየጨመረ በመምጣቱ ስርጭቱ አሳሳቢ በመሆኑ ይህን ለመግታት ማህበረሰቡ የራሱን የመሪነት ሚና መጫወት ያለበት መሆኑን በመግለጽ የጤና ትምህርትን በማስፋፋትና በቫይረሱ ተጎጂ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን እንዲሁም በበሽታው ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናትን በፋይናንስና በቁሳቁስ በመደገፍ ተቋማት የራሳቸውን ኃላፊነት እየተወጡ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

አያይዘውም በዓለም ከ78 ሚሊየን ሰዎች በላይ በቫይረሱ የተያዙ መሆናቸውን፣ 39.6 ሚሊየን ሰዎች በቫይረሱ የሞቱ መሆናቸውን፣ 36.9 ሚሊየን ሰዎች ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው መሆኑን፣ 16 ሚሊየን ህጻናት በቫይረሱ የተያዙ መሆናቸውን፣ በየዓመቱ 2.5 ሚሊየን ሰዎች በቫይረሱ የሚያዙ መሆናቸውንና በየዓመቱ 1 ሚሊየን የሚሆኑ ሰዎች በቫይረሱ የሚሞቱ መሆናቸውን በመግለጽ በሌሎች በኤች አይ ቪ ኤድስ ርእሰ ጉዳዮች ላይ በቂ የሆነ ግንዛቤን ሰጥተዋል።

የስልጠናዉ ተሳታፊ በበኩላቸው ስርጭቱን ለመግታት የሚደረጉ የሚዲያ ቅስቀሳዎች ቀነሰዋል፣ የማህበረሱ የእርስ በዕርስ ግንኙነት ቀንሷል፣ቀጣይነት ያለውና ያልተቆራረጠ ግንዛቤ ሊፈጠር ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡





